በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ.ቁ.210520
ህዳር 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

**አመልካች፡** **አቶ ቃሲም እድሪስ - አልቀረቡም**

**ተጠሪ፡** **አቶ አብዱርሃማን ተማም- ጠበቃ አቶ ጌታቸው ማሞ-ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ በአመልካች እና በሌላ አንድ ግለሰብ ላይ በሲናና ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ጭብጥም ቦታና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተገለፀውን 200 ካሬ ሜትር ይዞታ በ1998 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ ተሰጥቷቸው በእጃቸው አድርገው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስደዉበት እና ግብር እየገበሩበት እያለ አመልካች እና ሌላኛው ግለሰብ ከይዞታው ላይ ምንም መብት ሳይኖራቸው በላዩ ላይ የነበረውን አጥር በማፍረስ ቤት ሰርተዉበት የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበው መቃወሚያው በብይን ውድቅ ተደርጓል፡፡ የአማራጭ የስረ ነገር ክርክሩ ይዘትም ለክሱ መሰረት የሆነው ይዞታ ከመንግስት አካል በህጋዊ መንገድ በሰነድ ተረጋግጦ የተሰጠኝ ይዞታዬ በመሆኑ ተጠሪ ከይዞታው ላይ መብት የላቸውም የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ስለይዞታው ከክፍሉ ይዞታ አስተዳደር ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበትን ይዞታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአሁን ተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኘን የይግባኝ ክርክር ከሰማ እና ስለ ይዞታው በድጋሚ ከዞን እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር በተወጣጡ ባለሙዎች በጋራ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክሰ የቀረበበት ይዞታ በ1998 ዓ.ም ለአሁን ተጠሪ በህጋዊ መንገድ ተሰጥቷቸው በዚሁ ይዞታ ላይ በ2002 ዓ.ም የይዞታ ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን፣ ተጠሪ በዚሁ ይዞታ ላይ ከ1999 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በስማቸው ግብር ሲገብሩበት የነበረ ስለመሆኑ በወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የቀረበው የክፍሉ መሬት አስተዳደር መግላጫ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙት የተጠሪ የሰው ምክስሮችም ይህንኑ ፍሬ ነገር ያረጋገጡ መሆኑን፣ ከዚህ አንጻፃር በይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃው ላይ የየዞታው አዋሳኝ አለመጠቀሱ የሰነዱን ህጋዊነት የሚያሳጣ አለመሆኑን፣ በሌላ በኩል ይኸው ይዞታ በ2007 ዓ.ም ለአሁን አመልካች ቀድሞ በነበራቸው 200 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ተጨምሮ በአጠቃላይ በ400 ካሬ ሜትር ይዞታ በሊዝ ውል የተሰጣቸው ስለመሆኑ ከክፍሉ መሬት አስተዳደር የተሰጡት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች የሚያሳዩ መሆኑን፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያሰሟቸው የሰው ምስክሮች ይዞታው በሊዝ ውል የተሰጣቸው ስለሆኑ ያረጋገጡ መሆኑን፣ ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አኳያ የግራ ቀኙ መብት የሚለየው በማስረጃ ምዘና መሆኑን፣ በዚሁ አግባብ የቀረቡትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በተናጠል መዝኖ የተቀበለበትን እና ያልተቀበለበትን ምክንያት ካሰፈረ በኋላ የአሁን ተጠሪ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ በህግ አግባብ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እያለ ይዞታው ለአሁን አመልካች የተሰጠበት መንገድ ህግና ስርዓትን ባልጠበቀ መንገድ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር አመልካች በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት በራሳቸው ወጪ አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 05/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ አመልካች ከሚመለከተው አካል ጋር በተደረገ የሊዝ ውል የተረከቡ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ እንዲሁም ለተጠሪ የተሰጣቸው ማስረጃ የመሬቱን ልዩ ቦታ ስም የማያሳይ ስለመሆኑ የመንግስት አካል በማጣራት ያሳለፈውን ውሳኔ ስር ፍ/ቤት የሻረበትን አግባብነት ከመሰረታዊ የክርክር አመራር እና ከማስረጃ ምዘና መርህ አኳያ ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚመነጨው ከፌደራሉ ህገ መንግስት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 78 ይደነግጋል፡፡ በህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) መሰረት በፌደራልም ሆነ በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ለሚቋቋም የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን ነው፡፡ ህገ መንግስቱን መሰረት አድርገው በፌደራልም ሆነ በየክልሉ የታወጁት የፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጆችም በህግ መንግስቱ በተገለፀው አግባብ ተመሳሳይ የዳኝነት ስልጣን ለሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡ ለመሆኑ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ድንጋጌ እንዲሁም አሁን ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ካለው ከተሻሻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 216/2011 አንቀጽ 26(1) ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በፌዴራልም ሆነ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የተቋቋመው የሰበር ሰሚ ችሎት በህግ መንግስቱ እና ህገ መንግስቱን ተከትለው በወጡ አዋጆች የተሰጣቸው የሰበር ሰሚነት ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርጉ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋናነት መነሻ የሚያደርጉት ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡ እናም የሰበር ችሎት ቀዳሚ ተግባር የሚሆነው የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ የተረጋገጠውን መሰረት በማድረግ በሰጡት የህግ ትርጉም ውስጥ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ለይቶ በህግ አግባብ ማረም ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት ተመዝኖ አቋም የተያዘበትን ጉዳይ በተመለከተ በራሱ ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው የህግ አግባብ የለም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረው በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጡትን እንዲሁም በራሱ ማጣሪያ ትዕዛዝ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ነገሮች መሰረት በማድረግ ባከናወነው የማስረጃ ምዘና ስለመሆኑ በፍርድ ሀተታው ላይ በግልፅ አስፍሯል፡፡ ይህ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀመው ስህተት ከተገኘ ብቻ ስለመሆኑ ከላይ ስለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የዳኝነት ስልጣን ከሚዘረዝሩት ህግጋት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከማስረጃ ምዘና አንፃር የስር ፍርድ ቤት የፈፀመው የምዘና መርህ ጥሰት ስለመኖሩ የቀረበው የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ይህ ችሎትም ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት የማይቻል በመሆኑ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/375991 ላይ ሰኔ 29/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ፅ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም